# ጻፊ ጻፊና መጨረሻው ከንቱ!

# (መልስ ለይታያል የሩቅሰው )

ጌታቸው ዳግማዊ

አቶ ይታያል የሩቅ ሰው በ 4 ተከታታይ ጽሁፎች በኤርትራ ተይዞ ደብዛው የጠፋውን የኮለኔል ታደሰ ሙሉነህን ሰቆቃና ታሪክም ሊያቀርብልን ምክሯል። ደግ ነው ። ጸሓፊው ባይጠቅሰውም የኮለኔሉን ጉዳይ ከዚህ ቀደም የኢትዮጵያ የፖለቲካ እስረኞች አንድነት ኮሚቴም አንስቶ አቅርቦልን ነበር ። ከሁሉም፤ በፊት ደብዛው ስለጠፋው ኮለኔል ታደሰ ተቃውሞን ማሰማት ተገቢና ማድረግ ያለብን መሆኑን መጥቀስ ያስፈልጋል ።

ግን አቶ ይታያል የተረኩት ታሪክ ከሃቅ የራቀ መሆኑን መጥቀስ ያስገደደኝ ደግሞ በመደምደሚያው ኢሳያስ ኣፈወርቂን እንለምነው በሚል ስለ አስመራው አምባገነን ሊሸጥልን የሞከረው የሀሰት ግምገማ ነው ። ኮለኔል ታደሰ በዘመነ ደርግ የደህንነት መኮንን ሆኖ በአየር ሀይሉ ውስጥ የደህንነትና የ ኢሰፓ ኮሚሳርነት ስራ የሰራ በመሆኑ የስራ ባልደረቦቹ የሚወዱት ሰው አልነበረም። ኮለኔል ታደሰ በራሱ ጥረት ከተሰደደበት ናይሮቢ ወደ ዩጋንዳ የሄደ ሳይሆን ዛሬ በሕይወት የሌለ አቶ ዳንኤል ገብረ መድህን በተባለ ኢትዮጵያዊ አማካይነት ነው ። በዚያም ማንም የተቀበለው ስላልነበረ ኑሮው ከባድ መሆኑ ተነግሯል ። ሌሎች የአየር ሀይሉ ባልደረቦች በተደራጀ መልክ ወደ ዩጋንዳ ካምፓላ ተወስደውና በመንግስት ቤትና ጠባቂ ሲሰጣቸው አሁንም ሀገር ወዳድ ዜጎች ለምነውለት ኮልኔል ታደሰ ከእነሱ ተደባለቀ። ሊታገል ሳይሆን አቶ ይታያል ሊለው እንደፈለገው ከወያኔ ጋር አብሮ ሊሰራም ጓደኞቹን ትቶ ወደ አዲስ አበባ ዘለቀ፡፤ በዚያም ለወያኔ ሊሰራ ጀምሮ የቀደሞ ወዳጁ በኩረጽዮን (የ ኤርትራ አየር ሀይል ሃላፊ) ወደ አስመራ አባብሎ ለስራ ወሰደው ። እዚያ እየሰራ ሳለ (ኋላም ማቹ ኮለኔል ወጋሪ ተደባልቆታል ) የባድሜ ጦርነት ፈነዳና ኮልኔል ታደሰ ለወያኔ አየር ሀይል ባልደረቦች ከአስመራ ራዲዮ የአምጹ ጥሪ አስተለልፎ የአስመራ ስደተኛ ሆኖ ሕይወቱን ጀመረ።

ስለ አርበኞች ግንባር አመሰራረትና ሂደት ከሚቹ  ጌታቸው ተስፋዬም ሆነ ከኮማንደር መስከረም የምናውቅ በመሆኑ የይታያልን ትረካ ሚዛናዊ ሆኖ አላገኘሁትም ። ይህም ይቅር ። ኮለኔል ታደሰ የአስመራ መሳሪያ ሆኖ ከኮልኔል ሙሴ ጋር ሰምሮ መስራቱ የታወቀ ጉዳይ ነው ። ለወጣት ጌታቸው መታሰር፤ መደብደብና መገደልም የሚጠየቀው እንዳለ የግንባሩ አባላትና የሚቹ ዘመዶች ያውቃሉ ። ያም ሆኖ ይህ የአስመራው ቡድን በፈለገው ጊዜ ኮለኔሉን ኣግልሎታል ። ኮልኔል ታደሰ አሜሪካ በዘለቀ ጊዜም ከሚናገረው የተሰማው ሁሉ ምንኛ ኮለኔሉ የኢሳያስ ቲፎዞ እንደሆነ የሚያስረዳ ነበር ማለትም ይቻልል። ሆኖም ኮልነል ታደሰ ለምን ተያዘ፤ ለምንስ ደብዛው ጠፋ ብሎ መቆሮቆር፤ መጠየቅና ተቃውሞ ማሰማት ግዴታችን ነው ።

ይነጋል በላቸው በ ቁጥር 4 ጽሁፉ ግን ሁሉን/ አደባለቀውና ስለማንነቱም ጥርጣሬ ሊከተን ችሏል ። የይታያል ጽሁፎች ሲወጡና ኢፖአአኮም መግለጫ ሲወጣ አንድ ሀገር ወዳድ ዜጋ በኤርትራ ኤምባሲዎችና ኮንስሎች ደጃፍ የተባበረ ሰልፍ እናድርግ ብሎ ያደረገውን ጥሪ ይነጋል መልስ ብሎ አይጠቅምም ሲል ያሽቀነጠረና የኮለኔሉን መታሰር ወይም ደብዛው መጥፋት ጉዳይ ኢሳያስ አያውቅምና የይፈታ ፊርማ ሰብስበን ለየኤምባሲው እናቅርብና ሽማግሌዎችም ወደ አስመራ ወደ አምባገነኑ እንላክ ይላል ። ኮለኔሉ ይፈታልን ብሎ በ አንድ በኩል እንቅስቃሴ ይጋብዝና በሌላ በኩል ደግሞ ኢሳያስን አትወጥሩት አታሳፍሩት የተደረገውን አያውቅምና ብሎ መከራከር የ ይታያልን ማንነት ራሱን በጥያቄ ያስገባል ።  ይታያል የሩቅ ሰውም ይህን ያህል ስለ ኤርትራው አምባገነን አያውቅም ብሎ መገመትም ያዳግታል ። ኮለኔል ታደሰን ለማሰር ኮለኔል ሙሴ (ተሰነይ-ጉልች) ወይም ጀኔራል ጠኣመ ወዲ መቀሌ የሚያዙት ጉዳይ አይደለም። ቢያደርጉት እንኳን ኢሳያስን ያሳውቃሉ፤ ፈቃድም ይጠይቃሉ ። በኤርትራ ምድር አምባገነኑ የማያዘው ወይም የማያውቀው እስርና እንግልት ወይም ግድያ የለም። ይህ በዓለም አቀፍ ደረጃ የታውቀ ጉዳይ ሆኖ ሳለ የይታያል "እሳቸው  አያውቁም " ከአስገራሚም በላይ አጠያያቂ ነው ።

ምን መደረግ አለበት?

አንደኛ/ የይታያልን አፍቅሮ ሻዕቢያ ጥሪ ጆሮ አለመስጠት፤

ሁለተኛ/ የኮለኔል ታደሰን ደብዛ መጥፋት ምክንያት አድርጎ የኤርትራ ኤምባሲዎች ደጃፍ የተቃውሞ ሰልፎችን ማካሄድ፤

ሶስተኛ/ አለም አቀፍ አካላትም ይህን ተቃውሞ እንዲደግፉ ጥሪ ማስተላለፍ። ኣሳሪውን ለምኑት የተደረገውን አያውቅምና ጥሪ ግን የራሱ የሻዕቢያ ጥሪ ይመስላልና ይታያል አዛኝ ቅቤ ኣንጓች መስሎ የሚታየው ለዚህ ነው ።